# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 305 መጋቢት 5 2006


የእህቶቻችን በድፍረት ድምፃችሁን ማሰማት ያለው ትርጉም ከድምፃችሁ ከፍታ እና ከቁጥራችሁ በላይ ነው። ዛሬ ጥቂት እንኳን ብትሆኑ ነገ ብዙዎቻችን አርዓያነታችሁን እንድንከተላችሁ ያደርገናል። እናም እህቶቻችን በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ባሳያችሁን ድፍረት ተበረታተናል። ኢትዮጵያ ብሩህ ራዕይ ያላት፤ ቆራጥነትን የተላበሱ ወጣቶች ያሏት መሆኑን አሳይታችናል። ይህ ትንሽ ጅምር የትልቅ ሕዝባዊ ማዕበል መንገድ አመላካች ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የሀረር ሕዝብ በሀረር መንገዶች ከወያኔ ፌደራል ፖሊሶች ጋር ተፋጦ መዋሉ ተሰማ

በሀረር ከተማ በተለምዶ ሸዋ በር በሚባለው አካባቢ ለሁለተኛ ጊዜ የተከሰተውን የእሳት ቃተሎ በመቃወም የሀረር ከተማ ሕዝብ በነቂስ በመውጣትና መንገዶችን በመዝጋት በከፍተኛ ሁኔታ ተቃውሞውን ሲገልጽ ዋለ።

በድህነትና በብዙ መከራ  የፈራነው ሃብታችን የእሳት እራት ሆነ የሚሉት አንዳንድ ተቃዋሚዎች "ምነው ገዥዎቻችን ግብር ለመሰብሰብ ጊዜና ለምርጫ ብቻ ያስታውሱናል? እሳቱን ለማጥፋት እንኳ እንዴት በፍጥነት መድረስ ተሳናቸው? ይህ በእርግጥ ግፍ አይደለም!!" በማለት ስሜታቸውን እየታገሉ ሲገልጹ  ሌላኛው በተቃውሞው ቦታ የተገኙ የከተማው ኗሪ ደግሞ "ከዚህ የእንጀራችን መሰረት፣ ልጆቻችን ማሳደጊያ ከሆነው የንግድ ቦታችን እኛ በማናውቀው ምክንያት ለቀን እንድንወጣ በተደጋጋሚ አስጠንቅቀውናል፣ ቃጠሎው መነሳቱን የሚያውቁት የሀረር የወያኔ በድን የእሳት አደጋ ብርጌዱ በቶሎ መጥቶ እሳቱን እንዳያጠፋ እንቅፋት ሆነዋል። ይህም የሚያሳው ቃጠሎውን ሆን ብሎ ያስነሳው የሀረር ገዥ ወያኔ ነው" ማለታቸውን ዘጋቢአችን ከስፍራው ጠቁማል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የእሳት አደጋ ሰራተኞች ዘግይተው በመድረሳቸው የተነሳ እጅግ ከፍተኛ ሀብት እንደወደመ የጠቀሰው ዘጋቢያችን ተቃውሞው ጠንካራ በመሆኑ ማንኛውም አይነት የንግድም ሆነ ማሕበራዊ እንቅስቃሴ ታቅቦ መዋሉንና  የቢሮ ስራም ሆነ ትምህርት ቤቶች ተዘግተው መዋላቸውን ጨምሮ ጠቅሷል።

ከዚህ በፊት በአዲስ አበባ ከተማ በቂርቆስ፣በጎፋ ማዞሪያ፣ በኮልፌና በአቧሬ የንግድ መነሃሪያ ሰፈሮች ቦታውን ለራሳቸውና ለፋሽስት ወያኔ ተላላኪዎች ለማከፋፈል ሲባል ብቻ ፋሽስት ወያኔ የተቀነባበሩ ቃጠሎዎችን ሲያካሂድ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን በእነዚህ በሁሉም ቃጠሎዎች የአዲስ አበባ የእሳት አደጋ ብርጌድ ከተለመደው ጊዜ እጅግ በጣም ዘግይቶ መድረሱ መዘገቡም አይዘነጋም።

## የፋሽስት ወያኔን የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ የተቃወመ ታላቅ ሩጫ ተካሄደ

ባለፈው እሁድ በተደረገው የሴቶች ታላቅ ሩጫ ላይ ተሳታፊ የነበሩ ወገኖቻችን የወያኔ ሕወሃትን ከፋፍለህ ግዛ አካሄድ በጽኑ ማውገዛቸው ተሰማ። ሩጫው ከተጀመረ ጀምሮ እስከፍጻሜው ድረስ የቀጠለው ይህ ታላቅ የተቃውሞ ሩጫ ብዙ ማህበራዊ ህጸጾችን የነካኩና ወቅታዊ የሕዝብ ጥያቄዎችንም ያጎሉ መፈክሮችን ሲያሰማ እንደዋለ ዘጋቢያችን ከስፍራው ጠቁሟል።

ኢትዮጵያ ሀገራችን አንድ ናት፣ አትከፋፍሉን፣ አንድ ሕዝብና ነፃነት፣ ነፃነት በማለት በከፍተኛ ድምጽ አካባቢውን ሲያናውጽ የዋለው ይህ ታላቅ የተቃውሞ ሩጫ በሀገር አቀፍ ደረጃ ባልተቀናጀ መልኩ እየተካሄዱ ካሉት የሕዝብ እምቢተኝነት እንቅስቃሴዎች አካል እንደሆነ ዘጋቢአችን ጨምሮ ገልጿል። የተቃውሞ ሩጫውን በመደነቅ ሲመለከቱ በነበሩ ቁጥራቸው በዛ ያሉ ዩአካባቢው መንገደኞች ፊት የሃይል እርምጃ ለመውሰድ ተቸግሮ የዋለው ፋሽስት ወያኔ በሩጫው መጨረሻ ላይ የተወሰኑ የተቃውሞ ሩጫው አባላትን ማሰሩም ታውቋል።

የታሰሩት የፖለቲካ እስረኞችን፣ ነፃ ጋዜጠኞችንና የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴዎችን ስም እየጠሩ ባስቸኳይ እንዲፈቱ ሲጠይቁ የዋሉት እኒሁ የተቃውሞ ሩጫው ተሳታፊዎች "ምሬታችን ሞልቶ ፈሰሰና  ወያኔ ከዚህ በላይ በዚህ መልኩ ሊገዛን አይችልም" ማለታቸው የተሰማ ሲሆን በቀጣይም የዚሁ ቀጣይ የሆኑ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን በከፍተኛ ቁርጠኛነት እንደሚተገብሩ በጊዜው ማሳወቃቸውን ባልደረባችን ከስፍራው ጠቁሟል። ባልደረባችን በጉዳዩ ዙሪያ ያነጋገራቸው አንዳንድ ታዛቢዎች እየተደረጉ ያሉትን ጠንካራና ወቅታዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች የአተገባበር ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## አንድነት ፓርቲ የሚሊዮኖችን ድምጽ ዘመቻዉን እንደገና ሊጀምር ነው

አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ባለፈዉ አመት በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች አካሂዶ መልካምና የሚያበረታታ ልምድ ያገኘበትን "የሚሊዮኖችን ድምጽ" የተሰኘ ዘመቻዉን ለሁተኛ ግዜ ለማካሄድ በዝግጅት ላይ መሆኑን የፓርቲዉ ጽ/ቤት አሳወቀ። የፓርቲው ጽ/ቤት ባወጣው መግለጫ ለሦስት ወራት በሚካሄደው ክፍል ሁለት "የሚሊዮኖች ድምፅ ለመሬት ሪፎርም" በሚለው ዘመቻ፣ በዋነኛነት በተመረጡ 14 ከተሞች እና በሦስት ተጓዳኝ ከተሞች ሰላማዊ ሰልፍና ህዝባዊ ስብሰባ ይካሄዳል።

የመሬትን አጀንዳ የሁለተኛው ዙር የመታገያ አጀንዳ ለምን እንዳደረገ ፓርቲው ሲያብራራ፣ "በባለሃብት ስም ገበሬው ከይዞታው መፈናቀሉ፤ በከተሞች በልማት ስም ዜጎች እየተፈናቀሉ ለጎዳና ላይ ኑሮ መዳረጋቸው፤ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መበቶቻቸው እየተጣሱ ለማህበራዊ ቀውስ መዳረጋቸውው ዛሬም ተጠናክሮ መቀጠሉንና በተበጣጠሰ ትንንሽ የመሬት ይዞታ ላይ በኃይል የመፈናቀል ተራቸው እስከሚደርስ እየተጠባበቁ ያሉትም ቢሆኑ ዛሬም በዶማ እና በበሬ አፈር እየገፉ ከአቅማቸው በላይ በሆነ የማዳበሪያ እዳ ተቀፍድደው አንገታቸውን ደፍተው በሰቀቀን ለመኖር ተገድደዋል" ብሎአል።

"መሬትን ዋነኛ የሙስና ማዕከል ያደረገውን ሥርዓት በመቃወም የህዝብ የለውጥ ፍላጎት እንዲከበር አደባባዮች በለውጥ ፈላጊ ሰላማዊ ታጋይ ህዝብ እንዲሞሉ እንዲሞሉ ለማድረግ እንደሚንቀሳቀስ የሚገልጸው አንድነት፡ አምባገነናዊ ሥርዓቱ በሰላማዊ ትግል ተሸንፎ ዜጎች የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤት እንዲሆኑ፤ ሃብት የማፍራት፤ የመያዝ እና የማስተላለፍ መብታቸው እንዲጠበቅ፤ በኮሚኒቲ /በማህበረሰብ/ በጋራ ከተያዘ፤ በመንግስት ይዞታነት ከተከለለ እና በተቋማት ይዞታነት ከታወቀ መሬት በቀር በዜጎች የተያዘ መሬት የግል ይዞታ ሆኖ እንዲከበር ለማድረግ እንደሚታገል አስታውቋል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## 15 የቅማንት ብሄረሰብ አባላት ታሰሩ 14ቱ የደረሱበት አልታወቀም

በአማራ ክልል በሰሜን ጎንደር ዞን በጭልጋ፣ በአርማጭሆና በመተማ ወረዳዎች እና በአካባቢው ያሉ የቅማንት ብሔረሰብ አባላት እያቀረቡ ያለውን የማንነትና ህገመንግስታዊ ጥያቄ ለማፈን ሰሞኑን በድምሩ 29 ያህል የቅማንት ተወላጆች መታሰራቸውንና መታፈናቸውን የቅማንት ብሔረሰብ የማንነት ጥያቄና ራስ አስተዳደር ይፈቀድልኝ አስተባባሪ ኮሚቴ አስታውቋል።

ኮምቴው ከየካቲት 28 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ መልክ የቅማንት ብሔረሰብ ተወላጆች ላይ ያነጣጠረ እስርና አፈና መጀመሩን ይፋ አድርጓል። በዚሁ መሰረት ከጭልጋ 15 ሰዎች መታፈናቸውን፣ከላይ አርማጮህ 14 ሰዎች መታሰራቸውን በመግለጽ እርምጃው የታሳሪዎችን ደህንነት የጎዳ፣ ቤተሰባቸውን ለችግር ያጋለጠ፣ የብሔረሰቡንም ማህበራዊ ማንነት ያናጋ በመሆኑ ድርጊቱ እንዲቆምና የታሰሩትና የታፈኑት እንዲፈቱ የካቲት 28 ቀን 2006 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ ጠይቋል። የቅማንት ህዝብ በተበታተነ መልኩም ቢሆን በጭልጋ፣ በጎንደር ዙሪያ፣ በደንቢያ፣ በደጋው ቋራ፣ በላይ አርማጭሆና በመተማ የሚኖር ነው።ገዢው ፓርቲ ከጥያቄው ጀርባ እጁ አለበት እየተባለ አስተያየት ሲሰጥ ቢቆይም፣ አሁን የተወሰደው እርምጃ ይህን የሚያጠናክር ሆኖ አልተገኘም። በቅርቡ በጎንደር ከተማ በ100 ሺዎች የሚቆጠሩ የብሄረሰቡ ተወላጆች የተቃውሞ ሰልፍ አካሂደው ነበር። የፌደሬሽን ምክር ቤትም ጉዳዩን እያጠናው መሆኑን ተናግሯል።

## ሀረር ዉስጥ የደረሰዉን ቃጠሎ የተቃወሙ በርካታ ወጣቶች ታሰሩ

ባለፈዉ እሁድ ምሽት ሀረር ከተማ ዉስጥ ሳይታሰብ በድንገት የደረሰዉንና የብዙ ንብረት መዉደም ምክንያት የሆነዉን የእሳት ቃጠሎ በመቃወም አደባባይ የወጡ የከተማዋ ነዋሪዎች በፖሊስ ኃይል ከተበተኑ በኋላ ፖሊስ ለግዜዉ ቁጥራቸዉ በዉል ተለይቶ ያልታወቀ ወጣቶችን ማሰሩን ምስራቅ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢዎች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩልን ዜና ገለጹ። እንደ ዘጋቢዎቻችን አባባል የሀረርና የአካባቢዉ ፖሊሶች  በየመንገዱ ላይ ያገኟቸውንና እንዲሁም ከየቤታቸው እአቸዉን እያሰሩ ያወጧቸዉን ሰዎች ወደ እስር ቤት ወስደዋቸዋል።

የክልሉ አስተዳዳሪ አቶ ሙራድ አቡደላሂ የተወሰኑ ሰዎች ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በዓለም ዓቀፍ የሴቶች ቀን ዝክር፤ በእህቶቻችን ኮርተናል!!!

ለዘንድሮው ዓለም ዓቀፍ የሴቶች ቀን መታሰቢያ በአዲስ አበባ ከተማ በተደረገው የሩጫ ትዕይንት ላይ ወጣት ሴቶች ባሳዩት ልበ ሙሉነት ኮርተናል። የሩጫውን ትዕይንት አስታከው፣ በአብዛኛው የሰማያዊ ፓርቲ አባላት እንደሆኑ የተነገረላቸው ወጣት ሴቶች ለፍትህ፣ ለነፃነት፣ ለህሊና እስረኞች መፈታት እና ለሀገር አንድነት ድምፃቸውን ከፍ አድረገው ጮኸዋል፤ ዘምረዋል። እነዚህ ወጣት ሴቶች በሥርዓቱ ምን ያህል እንደተማረሩ በቃላትም በአካል ንቅናቄም አሳይተዋል። ዘረኛውና ፋሽስቱ ወያኔ ግን "ለምን ተቃወማችሁኝ" ብሎ አስሯቸዋል፤ ከፊሎቹም የደረሱበት አይታወቅም። በእህቶቻችን ቆራጥነት ኮርተናል፤ በወያኔ የፈሪ ዱላ ደግሞ ተቆጥተናል። በ1997 እና 98 "የወላጆቻችን ድምጽ ይከበር" ያሉ ሕፃናትን የጨፈጨፈው ወያኔ በ2006 ወጣት ሴቶችን ከማሰቃየት ይመለሳል ብለን አናምንም። ወያኔ እስካልተወገደ ድረስ የፈሪ ዱላው የማይቀር ነገር ነው።

የወንዶቹን ያህል የተዘገበ አይሁን እንጂ በክፉም በደጉም ሴቶች ያልተሳተፉበት የኢትዮጵያ ታሪክ የለም። የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን እንኳን ብናይ በፋሽስት ወረራ ወቅት ኢትዮጵያዊያን ሴቶች በአርበኝነት ዘምተው አዋግተዋል፤ ተዋግተዋል። በተለያዩ ምክንያቶች መዝመት ያልቻሉት ደግሞ በውስጥ አርበኝነት ተሰልፈው የጠላት ምስጢሮች ለአርበኞች እንዲደርሱ በማድረግ ከፍተኛ ጀብዱዎችን ፈጽመዋል። ከፋሺስት ወረራ ወዲህ በነበሩ ዓመታት ውስጥም ለፍትህ እና ለነፃነት በተደረጉ ተጋድሎዎች ሴቶች ጉልህ ተሳትፎ ነበራቸው። በተማሪዎች ትግል ውስጥ ለምሳሌ፣ ወጣት ሴቶች በአመራር ደረጃ በመሳተፍ ትግሉን መርተዋል፤ የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር ከፍለዋል። ከዚያ ወዲህም በነበሩት ዓመታት በኢሕአፓ እና ሌሎችም ድርጅቶች አመራርና አባልነት ተሳትፈው ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረጉ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች ነበሩን። በቅርቡም በምርጫ 97 እንቅስቃሴም የሴቶች በተለይም የወጣት ሴቶች ተሳትፎ ምን ያህል ጉልህ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነውና እናስታውሳለን። ለምርጫ ድምጽ መከበር ወጣት ሽብሬ ደሣለኝን ጨምሮ በርካታ ሴቶች ሕይወታቸውን ሰውተዋል፤ ከዚያ የበለጡት ደግሞ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። ዛሬም እንደ ርዕዮት ዓለሙ የመሳሰሉ ጀግኖች በወያኔ ወህኒ ቤቶች እየማቀቁ፤ በየእለቱ ሰቆቃ (ቶርቸር) እየተፈፀመባቸው መሆናቸው በሀዘንና በቁጭት እናስባቸዋለን።

በሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ አስፈላጊነት በመፈክር ደረጃ አንስተን የምንተወው ጉዳይ አይደለም። የሴቶች ተሳትፎ ያልታከለበት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ግቡም አይመታም፤ ቢመታም ዋጋ የለውም።

ከጥቂት ዓመታት በፊት የተካሄዱትን የሰሜን አፍሪቃና የመካከለኛው ምሥራቅ አብዮቶችን በአንክሮ የተከታተለ ማንኛውም ሰው ከሚገረምባቸው ነገሮች አንዱ ሴቶች ያሳዩት ቆራጥነት እና ያካሄዱት ብስለት የተሞላው ትግል ነው። በቱኒዚያ የወጣቶች እንቅስቃሴ ውስጥ ወጣት ሴቶች ከመጀመሪያው ጀምሮ የአመራር ቦታ በመያዝ ተሳትፈዋል። በግብጽም የወጣት ሴቶች እልህ ከወንዶቹ በልጦ ታይቷል። አሁን በዩክሬን ውስጥ የምናየው ሀቅም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው።

የሴቶች በሕዝባዊ አብዮቶች በስፋት መሳተፍ ከቁጥር ማብዛት እጅግ የላቀ መሠረታዊ ጠቀሜታዎች አሉት። ጥቂቶቹን እንደሚከተለው መዘርዘር ይቻላል።

1. ለሴቶች ያልተመቸ ሥርዓት ለማንም አይመችም። ለማኅበረሰብ በጠቅላላ የሚመች ሥርዓት መገንባት ማለት በቅድሚያ ለሴቶች የሚመች ሥርዓት መገንባት ማለት ነው። ይህ ሥርዓት ደግሞ እነሱ እራሳቸው እየተሳተፉበት፤ ከዚያም አልፎ እየመሩትም ነው መገንባት ያለበት።
2. ሴቶች ከወንዶች በላይ ታጋሾች ናቸው፤ ሲያመሩ ደግሞ በቀላሉ አይመለሱም ተብሎ ይታመናል። እናም የሴቶች በተቃውሞ ትግል ውስጥ በብዛት መሳተፍ ሥርዓቱ በሕዝቡ ምን ያህል እንደተጠላ ግልጽ አመላካች ነው።
3. የወጣት ሴቶች በድፍረት ለተቃውሞ አደባባይ መውጣት ወጣት ወንዶችን ያጀግናል። የወጣት ወንዶች መጀገን ደግሞ ወጣት ሴቶቹን ይበልጥ ያጀግናል። ወጣት ሴትና ወንዶች በእርስ በርስ አርዓያነት ይጀጋገናሉ። እናም ወጣት ሴቶች አምረው ተነሱ ማለት ሁሉም ወጣቶች ሁሉ አምረው ተነሱ ወደማለት ያመራል።
4. የእናቶች መቁረጥ አባቶችን ያነሳሳል፤ የእናትም የአባትም መነሳት ደግሞ መላው ቤተሰብ በሥርዓቱ ላይ እንዲነሳ ያደርገዋል። እናም እናቶች አመረሩ ማለት መላው ቤተሰብ አመረረ ማለት ይሆናል።
5. የሴቶች በትግል አመራር ቦታ ላይ መገኘት በተቃዋሚዎች መካከል ኅብረትን፣ መተሳሰብን ባጠቃላይም ቤተሰባዊ ስሜት ይፈጥራል።
6. ሴቶችና ወንዶች አብረው ሲቆሙ ነው የመተባበር ጥቅም በጉልህ የሚታየው!

የእህቶቻችን በድፍረት ድምፃችሁን ማሰማት ያለው ትርጉም ከድምፃችሁ ከፍታ እና ከቁጥራችሁ በላይ ነው። ዛሬ ጥቂት እንኳን ብትሆኑ ነገ ብዙዎቻችን አርዓያነታችሁን እንድንከተላችሁ ያደርገናል። እናም እህቶቻችን በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ባሳያችሁን ድፍረት ተበረታተናል። ኢትዮጵያ ብሩህ ራዕይ ያላት፤ ቆራጥነትን የተላበሱ ወጣቶች ያሏት መሆኑን አሳይታችናል። ይህ ትንሽ ጅምር የትልቅ ሕዝባዊ ማዕበል መንገድ አመላካች ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ዘረኛውንና አምባነኑን ወያኔ ከጫንቃችን ለማውረድ በምናደርገው ትግል የእህቶችና የእናቶች ተሳትፎ ወሳኝ እንደሆነ ያውቃል፤ ስለሆነም ሴቶች ትግሉን በስፋት እንዲቀላቀሉ ጥሪ ያደርጋል። ሴቶችና ወንዶች፤ ወጣቶችና አረጋዊያን ሁላችንም የወያኔን ዘረኛ አገዛዝን እንዲያበቃ በጽናት እንታገል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ባህር ዳርን ለቅቀዉ ወደ ክልል የሄዱ ታክሲ ሾፌሮች እየታሰሩ ነው

ባህር ዳርን ለቅቀዉ ወደ ተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች በመሄድ በታክሲ ሾፌርነታቸዉ ለመቀጠል የሞከሩ አንዳንድ የታክሲ አሽከርካሪዎች በወያኔ ፖሊሶች እየታደኑ በመታሰር ላይ መሆናቸዉን አንድ ስማቸዉ እንዳይገለጽ የጠየቁን የታክሲ ሾፌር ለዝግጅት ክፍላችን በስልክ ገለጹ። ከባህርዳር ከተማ ወደ ሌሎች ክልሎች ተዘዋውረው በመስራት ላይ ያሉ እነኚሁ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ የታክሲ አሽከርካሪዎች መታሰ ብቻ ሳይሆን እስከ 10 ሺ ብር የሚደርስ ቅጣት እንዲከፍሉ እየተደረገ ነው።

በአገራችን እንደልባችን ከክልል ክልል ተዘዋውረን እንዳንሰራ በፖሊሶች ታግደናል የሚሉት ሾፌሮች፣ ለምን ብሎ የጠየቀ ሰው ድብደባ እንደሚፈጸምባቸው ይናገራሉ በሌላ በኩል ደግሞ በሸዋ ሮቢት ከተማ የሚገኙ የባጃጅና የታክሲ አሽከርካሪዎች ከአማራ ክልል ውጭ በመሄድ በሌሎች ክልሎች መንጃ ፈቃድ በማውጣታቸው፣ ክልሉ በህጋዊነት ሊቀበለው እንደማይችል በመግለጹ ስራ ማቆማቸውን ተናገሩ። ካለፉት 4 ቀናት ጀምሮ ተቃውሞዋቸውን እያሰሙ የሚገኙት የታገዱ ሾፌሮች ጉዳያቸውን ከክልል እስከ ፌደራል ባለስልጣናት ቢያቀርቡም መፍትሄ ሊያገኙ አልቻለም።

ሾፈሮቹ ችግራቸው በአስቸኳይ የማይፈታ ከሆነ የረሀብ አድማ እንደሚጀምሩ ተናግረዋል ።አንድ የክልል ሾፌር ወደ ሌላ ክልል ሄዶ መንጃ መፈቃድ ለማውጣት እንደማይችል የሚደነግግ ህግ አለመኖሩን ለማወቅ ተችሎአል። የኢትዮጵያ ህገመንግስት ሰዎች ከቦታ ቦታ ተዘዋውረው መስራት እንደሚችሉ ቢደነግግም ይህ ሙብት በብዙ ክልሎች እየተጣሰና ክልሎች ራሳቸውን እንደ አገር በመቁጠር ማስተዳደር መጀመራቸውን የሚመለከቱ ትችቶች ይቀርባሉ። መንግስት በበኩሉ በቋንቋና በዘር ላይ የተመሰረተው የፌደራል ስርአት የአገሪቱን አንድነት አስጠብቋል፣ ግጭቶችንም ለማስወገድ አስችሎአል ብሎ ይከራከራል።

## በኢትዮጵያ ህጻናትን በማደጎነት የሚልኩ የውጭ ድርጅቶች ዘመቻ ሊጀምሩ ነው

የወያኔ አገዛዝ በቅርቡ ከኢትዮጵያ ወደ ተለያዩ አገሮች በጉዲፈቻ ስም የሚወጡ በርካታ ህጻናትን አስመልክቶ ያወጠዉን መመሪያ በመቃወም አንዳንድ ህጻናትን በማደጎነት ወደ ዉጭ አገር የሚልኩ ደድርጅቶች መመሪያዉን ለማስለወጥ ዘመቻ ሊጀምሩ እንደሆነ ታወቀ። እነዚህ ድርጅቶች በማህበራዊ ሚድያዎቻቸዉ የተለቀቀ አንድ የድምጽ ማስረጃ እንደሚያሳየው ህጻናትን በጉዲፈቻ ስም ወደ ውጭ አገራት የሚልኩ በተለይም የአሜሪካ ድርጅቶች የኢትዮጵያ መንግስት በቅርቡ ያወጣውን ህግ በመቃወም ዘመቻ ሊጀምሩ መሆኑን ውሳኔ ላይ ደርሰዋል።

የኤጀንሲው ተወካዮች እንደሚገልጹት፣ መንግስት በቅርቡ የጣለው እገዳ በመገናኛ ብዙሀንና በህዝቡ ተጽእኖ የመጣ ነው። አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት በቂ ገንዘብ እስከተከፈለ ድረስ የጉዲፈቻ ሂደቱ እንዲቀጥል እንደሚፈልጉ ይ አንድ አስተያየት ሰጪ የመቀሌ ባለስልጣናትን በማናገር ለመረዳት መቻሉዋን በውይይቱ ላይ ገልጻለች።

ህዝቡና ጋዜጠኞች ጉዲፈቻን በተመለከተ የያዙትን አቋም ለማስለወጥ ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የአየር ሰአት በመግዛት ውይይት እንደሚከፍቱ በመጨረሻ ባወጡት የአቋም መግለጫ ገልጸዋል።የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት " ህጻናትን በጉዲፈቻ ስም" ወደ ውጭ የማውጣቱን አሰራር እንደሚቃወም በውይይቱ ላይ የተነሳ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ መንግስት በቅርቡ በወሰደው እርምጃ በርካታ ድረጅቶች በገንዘብ እጥረት መቸገራቸውም ተገልጿል።ኢትዮጵያውያን ህጻናት ወደ ውጭ አገር እየተላኩ ከፍተኛ ስቃይ እየደረሰባቸው መሆኑ በተደጋጋሚ ተዘግቧል። ሃና ዊሊያምስ የተባለችው ኢትዮጵያዊት ታዳጊ በአሳዳጊዎቿ ከተገደለች በሁዋላ መንግስት ሂደቱ እንዲቋረጥ ማድረጉ ይታወቃል።

---

# አንድ ሰዉ ለማዳን አገር አይሞትም

እራሱን ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ህወሀት) በሚል ስያሜ ሰይሞ ለትግራይ ክልል ነፃነት የተዋጋዉ ወያኔ በለስ ቀንቶት አዲስ አበባን ሲቆጣጠር “ህወሀት” ተብሎ እየተጠራ ኢትዮጵያን መምራት እንደማይችል በሚገባ ያዉቅ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ገና ሲፈጠሩ ጥላቻና ጎጠኝነት የተጠናወታቸዉ የወያኔ መሪዎች የጎጥ ስማቸዉን መቀየር በፍጹም አልፈለጉም። ይህንን እንቆቅልሽ ለመፍታት ደግሞ መለስ ዜናዊና ስብሀት ነጋ የታያቸዉ ብዙ ማሰብና ጉዳዩ ከሚመለከተዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መምከር ሳይሆን እንደነሱ የማያስቡና አርቀዉ መመልከት የማይችሉ ግለሰቦችን ሰብስበዉ ቁመናዉና ቅርጹ ኢትዮጵያዊ ይዘቱና ትዉልዱ ግን ወያኔያዊ የሆነ ድርጅት መፍጠር ነበር። ይህንን ድርጀት ማለትም ኢህአዴግን ለመፍጠር ደግሞ መለኪያዉ የፓለቲካ መመሳሰል ሳይሆን እንደ ህወሀት እንደ እራሱ ዘር እየቆጠሩ መሰባሰብ ወይም እራስን እንደ ኢትዮጵያዊ ሳይሆን አንደ ትግሬ፤ አንደ ኦሮሞ፤ እንደ ሲዳማና እንደ አማራ መመልከት ነበር። ይህንን መመዘኛ ከግምት ዉስጥ በማስገባት ወያኔ ጠፍጥፎ ከሰራቸዉ ድርጅቶች ዉስጥ አንዱ የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ወይም አህዴድ ነዉ።

ይህ ኦሮምኛ መናገር በሚሞክሩ፤ ኦሮሚያ ዉስጥ በተወለዱና ወያኔ ጦር ሜዳ ላይ ማርኮ ወደ ኦሮሞነት በለወጣቸዉ ግለሰቦች የተፈጠረዉ ድርጅት በ24 አመት አመት የስልጣን ዘመኑ የወያኔ ተወካይ ሆነዉ ኦሮሚያን የመሩ አምስት አሻንጉሊቶች አፍርቶ ስድስተኛዉን ለማንገስ የወያኔን ቡራኬ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል። እነዚህ ኦሮሚያን በተከታታይ የመሩ አምስት ፕሬዚዳንቶች ለኦሮሞ ህዝብ መብትና ነፃነት መከበር ምን ሰሩ ለሚለዉ ጥያቄ መልሱ ምንም ስለሆነ እዚህ “ምንም” ዉስጥ ገብተን ምን ሰሩ የሚለዉን ጥያቄ ለመመለስ የምናጠፋዉ ግዜም ፍላጎትም የለንም። ሆኖም የወያኔን ተንኮልና ዘረኝነት ለማሳየት የአንዳንዶቹን የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንነት ተብዬዎች ማንነት ማሳየት ጠቃሚ ይመስለናል። ለምሳሌ ታዬ ተክለ ሐይማኖትን (በአሁኑ ስሙ) ኩማ ደመቅሳን ስንመለከት ይህ ሰዉ በወጣትነቱ ፖሊስ ሠራዊት ተመልምሎ ኤርትራ ዉስጥ በግዳጅ ላይ እያለ የተማረከ ሰዉ ነዉ። ኩማ ደመቅሳ በ1980ዎቹ የመጀመሪያ አመታት ህወሀትና ሻዕቢያ ባደረጉት የእስረኛ ልዉዉጥ ለወያኔ ከተሰጠ በኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄን (ኢህዴንን) ተቀላቅሎ በ1982 ዓም በወያኔ ቡራኬ ወደ ኦሮሞነት ተለዉጦ የዛሬዉን አህዴድን ከፈጠሩ ሰዎች አንዱ ነዉ። ኩማ ደመቅሳ በሙሰኝነትና በምግባረ ብልሹነት ተከስሶ ከኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንትነቱ ሲወገድ ሁላችንም የዚህ ማንነቱ የጠፋበት ሰዉ የፖለቲካ ህይወት ያከተመ መስሎን ነበር። ሆኖም የወያኔ ችግር የኦሮሞን ህዝብ ጥቅም ማን ያስከብራል የሚለዉ ጥያቄ ሳይሆን ኦሮሚያን ማን ረግጦ ያስገዛልኛል ነዉና በራሱ መለኪያ ወንጀለኞች ናችሁ ብሎ ከስልጣን ያባረራቸዉን አንደ ኩማ ደመቅሳን የመሳሰሉ ደካሞቸች እየደጋገመ ወደ ስልጣን ያመጣቸዋል።

ፈጣሪ ነብሳቸዉን ይማረዉና ስልጣናቸዉን በገዛ ፈቃዳቸዉ ለቀቁ ተብሎ ሁለት ሳምንት ሳይሞላ ዜና እረፍታቸዉ የተነገረዉ  አቶ አለማየሁ አቶምሳም ኦሮሚያን በፕሬዚዳንትነት እንዲመሩ ሲደረግ አላማዉ የኦሮሞን ህዝብ ይጠቅማሉ ተብሎ ሳይሆን ይልቁንም ዋናዉ አላማ የኦሮሞን ህዝብ ለወያኔ ለማስገዛት ነበር። የዛሬ ሦስት አመት አቶ አለማየሁ አቶምሳ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ሆነዉ ተሾሙ የሚለዉ የሹመት ዜናና አቶ አለማየሁ አቶምሳ ለህክምና ታይላንድ ሄዱ የሚለዉ ዜና-ህመም ለኦሮሞ ህዝብ የተነገረዉ አንድ ላይ ነበር። ለሚቀጥሉት ሦስት አመታት የኦሮሚያ ክልል ህዝብ አቶ አለማሁ አቶምሳ ዉሳኔ ወሰኑ፤ ስብሰባ መሩ ወይም የክልሉን በጀት ለፓርላማ አቀረቡ የሚል ዜና ሰምቶ አያዉቅም፤ አቶ አለማየሁ አቶምሳም ቢሆኑ በሦስት አመት የስልጣን ዘመናቸዉ የኦሮሚያን ክልል በፕሬዚዳንትነት በመምራት ካሳለፉት ግዜ ይልቅ ታይላንድ ሆስፒታል ዉስጥ በህክምና ያሳለፉት ግዜ በእጅጉ ይበልጣል።

ኦሮሚያን ያክል ትልቅ ክልል ለመምራት አንኳን ታይላንድ ሆስፒታል ዉስጥ ታምሞ የተኛ ሰዉ እዚያዉ ክልሉ ዉስጥ የሚኖር ሙሉ ጤነኛ ሰዉም አይኑን ለአንዲት ደቂቃም ቢሆን ከመሪነት ሀላፊነቱ ላይ ማንሳት የለበትም። ታድያ ለምንድነዉ አቶ አለማየሁ አቶምሳ በጠና መታመማቸዉ እየታወቀ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት እንዲሆኑ የተደረገዉ? ፕሬዚዳንት ሆነዉ ከተሾሙ በኋላስ አብዛኛዉን ግዜያቸዉን የሚያሳልፉት ታይላንድ ሆስፒታል ዉስጥ መሆኑ እየታወቀ ለምንድነዉ ሙሉ ጤንነት የሚጠይቅ ከፍተኛ የሀላፊነት ቦታ ይዘዉ እንዲቀጥሉ የተደረገዉ?
ባለፈዉ የካቲት አስር ቀን በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን  የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት የስልጣን መልቀቂያ ደብዳቤ አስገቡ ተብሎ ሲነገርና ፓርቲያቸዉ አህዴድም ጥያቄያቸዉን ተቀብሎ አጸደቀ ሲባል አቶ አለማየሁ አቶምሳ አንደኛ አገር ዉስጥ አልነበሩም ፤ ሁለተኛ በወቅቱ እሳቸዉ ደብዳቤ ጽፈዉ መልቀቂያ ሊጠይቁ ቀርቶ በራሳቸዉ መተንፈስም አይችሉም ነበር።

የአቶ አለማየሁ አቶምሳና ሌሎቹም የጤና መታወክ የደረሰባቸዉ የወያኔ ባለስልጣኖች ጉዳይ የሚያሳየን አንድ ትልቅ እዉነት ቢኖር በወያኔዋ ኢትዮጵያ ዉስጥ በደረጃ የሚበላለጡ የተለያዩ የዜግነት እርከኖች አንዳሉ ነዉ። ለምሳሌ ቱባ ቱባዎቹ የወያኔ ባለስልጣኖች እራስ ምታት እንኳን ሲይዛቸዉ እየሮጡ የሚሄዱት አዉሮፓና አሜሪካ ነዉ። እንደ አለማየሁ አቶምሳ አይነቶቹ ወያኔን እንዲያጅቡ የተጠሩ ሁለተኛ ደረጃ ዜጎች ደግሞ ሲታመሙ የሚሄዱት ታይላንድና ደቡብ አፍሪካ ነዉ። ከእነዚህ ዉጭ አገር ዉስጥ የህክምና አገልግሎት የሚያገኙ ዜጎችም በሁለት እርከኖች የተከፈሉ ናቸዉ፤ በመጀመሪያዉ እርከን ዉስጥ በራሳቸዉ ገንዝብ አገር ቤት ዉስጥ በሚገኙ የግል የጤና ተቋሞች የሚታከሙ በሦስተኛ ደረጃ የተቀመጡ ዜጎች ሲኖሩ ከእነሱ ቀጥሎ ደግሞ በየሆስፒታሉ የጤና አገልግሎት የሚያገኙ አራተኛ ደረጃ ዜጎች አሉ። ከዚህ ዉጭ ወያኔዎች ተራዉ ህዝብ እያሉ የሚጠሩት አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ህዝብ አለ፤ ይህ ህዝብ ደግሞ የረባ የጤና አግልግሎት አያገኝም ፤ ቢያገኝም የጤና ጣቢያ ፍለጋ የአንድ ቀን መንገድ በእግሩ መኳተን አለበት።

አቶ አለማየሁ አቶምሳ ህክምና ላይ በቆዩበት ሦስት አመታት ዉስጥ የኦሮሚያ ክልል መንግስት ከ38 ሚሊዮን ብር በላይ ለታይላንድ ሆስፒታሎች ከፍሏል። አንግዲህ በገጠማቸዉ ከባድ የጤና ችግር የተነሳ ክልሉን መምራት እንደማይችሉ በግልጽ እየታወቀ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ሆነዉ የተሾሙት አቶ አለማየሁ አቶምሳ ለክልሉ ምንም ስራ ሳይሰሩ ከሁለት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ የህክምና ወጪ ተደርጎላቸዋል። ይህንን ትልቅ ወጪ የከፈለዉ ደግሞ እሱ እራሱ የረባ ህክምና አገልግሎት አግኝቶ የማያዉቀዉ ደሃዉ የኦሮሞ ህዝብ ነዉ። ለመሆኑ የኢትዮጵያን ህዝብ ረግጠዉ የሚገዙት የወያኔ መሪዎችና ቡችሎቻቸዉ በብዙ ቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር የህዝብ ኃብት ዘርፈዉ በዉጭ አገር ባንኮች እያከማቹ ሲታመሙ ደግሞ በዚሁ ደሃ ህዝብ ገንዘብ ታይላንድና አዉሮፓ እሄዱ የሚታከሙት ለምንድነዉ? ደግሞስ ምድረ የወያኔ ሹም በየቀኑ ይታመማልና የኢትዮጵያ ህዝብ በምን እዳዉ ነዉ ጠግበዉ የሚረግጡት አምባገነኖች ሲታመሙ የሚያሳክማቸዉ?

የኦሮሚያ ክልል መንግስት በጠና መታመማቸዉ እየታወቀ ፕሬዚዳንት ሆነዉ የተሾሙትንና አንድም ቀን በሙሉ ችሎታቸዉ ክልሉን መርተዉ የማያዉቁትን አንድ ግለሰብ ታይላንድ ድረስ ልኮ ለማሳካም ከ38 ሚሊዮን ብር  በላይ ወጪ ማድረጉን በቅርቡ ይፋ አድርጓል። የተመድ የጤና ድርጅት በሚያወጣቸዉ መረጃዎች መሠረት ኦሮሚያ ክልል ዉስጥ አንድ ሆስፒታል አገልሎት የሚሰጠዉ ለአንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ሺ ሰዉ ነዉ፤ በሌላ በኩል ድግሞ እዚያዉ ኦሮሚያ ዉስጥ አንድ የሜዲካል ዶክተር ለ76 ሺ ሰዎች የጤና አገልግሎት ይሰጣል። እነዚህን ሁለት ቁጥሮች ወስደን የኦሮሚያ ክልል መንግስት አንድ ሰዉ ዉጭ አገር ልኮ ለማሳከም ካወጣዉ ወጪ ጋር ስናነጻጽር ወጪዉ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ደሃ ኢትዮጵያዉያንን ህይወት ማትረፍ የሚችል መሆኑን በቀላሉ መመልከት እንችላለን። 38 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር እያንዳንዳቸዉ 80 ሺ ዶላር የሚያወጡና የተሟላ የጤና አገልግሎት መስጠት የሚችሉ 25 የገጠር የጤና ተቋሞችን መስራት ይችላል። እነዚህ የጤና ተቋሞች እያንዳንዳቸዉ አንድ የሜዲካል ዶክተር ቢመደብላቸዉ ኦሮሚያ ክልል ዉስጥ አንድ የሜዲካል ዶክተር 76 ሺ ሰዎችን ስለሚደርስ እነዚህ ተቋሞች በትንሹ ለአንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ወይም 6 በመቶ ለሚሆነዉ የኦሮሚያ ክልል ነዋሪ የጤና አገልግሎት መስጠት ይችላሉ።

ኢትዮጵያ ዉስጥ እጥፍ ድርብ እድገት አመጣን፤ የብሄረሰቦችን እኩልነት አረጋገጥን፤ ወይም የኢትዮጵያ ህዝብ እራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር አስቻልነዉ እያሉ የሚፎክሩት የወያኔ ዘረኞች እራሳቸዉንና ያጀቧቸዉን ጥቂት ሆዳሞች ከመጥቀም ዉጭ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምንም እንዳላደረጉለት ይህ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ያሳዩት ፌዝ አይነተኛ ምሳሌ ቢሆንም የችግሩን ስፋትና ጥልቀት የማያሳይ ትንሽ ምሳሌ ነዉ። የወያኔ ሹሞች እንዴት በኢትዮጵያ ህዝብ ንብረትና ገንዘብ እንደሚቀልዱ እናዉራ ብንል እነሱን ለማስወገድ የምናደርገዉን የትግል ጉዞ ያርዝመዋልና አንሞክረዉም፤ ሆኖም አንዳንድ መነገር ያለባቸዉን ነገሮች ከመናገር ግን በጭራሽ ወደኋላ አንልም። ለምሳሌ ወያኔዎች ከ17 አመት የበረሃ ቆይታ በኋላ አዲስ አበባ ሲገቡ ፈትተዉ እንደለቀቁት ዉሻ በየመሸታ ቤቱ ሲልከሰከሱና በስም አንኳን ለይተዉ የማያዉቁትን መጠጥ ሲጠጡ  ሁሉም በበሽታ ተለክፈዋል። ለምሳሌ ስዩም መስፍን ሁሌም እንደታመመ ነዉ፤ ሳሞራ የኑስ ጤነኛ ሆኖ አያዉቅም ፤ በረከት ስምኦን ሁሌም ልቤንና ወገቤን አንዳለ ነዉ፤አባይ ፀሐዬም ስኳር ፋብሪካ ልከዉት ስኳር በስኳር ሆኗል። ታድያ ይህን ሁሉ በሽተኛ የኢትዮጵያ ህዝብ ዶላር ከዬት አምጥቶ ነዉ አዉሮፓና አሜሪካ እየላከ የሚያሳክመዉ?

እነዚህ የህዝብ ገንዘብ እየዘረፉ አዉሮፓና አሜሪካ ባንኮች ዉስጥ የሚያከማቹ፤ ልብሳቸዉንና የቤት ዉስጥ ዕቃዎቻቸዉን በዉድ ዋጋ ከዉጭ አገር የሚገዙ፤ ልጆቻቸዉን ዉጭ አገር እየላኩ የሚያስተምሩና ጉንፋን በያዛቸዉ ቁጥር ወደ ዉጭ አገር የሚሮጡ የወያኔ ባለስልጣኖች ለመሆኑ ኢትዮጵያ ዉስጥ ምንድነዉ የሚያደርጉት? ለምንድነዉ ህዝብን ከመዝረፍ፤ ከማሰርና ከመግደል ዉጭ ሌላ ምንም ስራ የሌላቸዉ ሰዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚኖሩት? በቀላል የህክምና ዕርዳታ ሊወገዱ በሚችሉ ትናንሽ በሽታዎች እንደ ቅጠል የሚረግፈዉ የኢትዮጵያ ህዝብስ ለምንድነዉ ለዚህ ችግር የዳረጉትን ነብሰ ገዳዮች ገንዘብ እየከፈለ በዉጭ አገር ሆስፒታሎች የሚያሳክመዉ ? ኢትዮጵያን በመሰለ ደሃ አገር ቀርቶ በዕድገት ወደፊት በገፉ

( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## አዲስ አበባ ዉስጥ በከፍተኛ ወጪ የተገነቡ ከ60 በላይ ቤቶችና ድርጅቶች ሊፈርሱ ነዉ

ከአዲስ አበባ አዳማ ድረስ ይሰራል ለተባለዉ መንገድ ቦታ ለማስለቀቅ ሲባል ነፋስ ስልክ አካባቢ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ዉስጥ የሚገኙ ከ60 በላይ ቤቶችና ድርጅቶች ሊፈርሱ ነዉ የሚለዉ ዜና ነዋሪዎችንና የክፍለ ከተማዉን አስተዳዳሪዎች እያጨቃጨቀ መሆኑን ከአዲስ አበባ የሚደርሱን ዜናዎች ያመለክታሉ።

አንዳንድ መኖሪያ ቤታቸዉ እንደሚፍርሰባቸዉ የተነገራቸዉ የላፍቶ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎች እንደተናገሩት፣ የመኖሪያ ቤቶችና የንግድ ተቋማትን ለመገንባት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጥያቄ ያቀረቡት በ1994 ዓ.ም. ነው። ጥያቄያቸው ተቀባይነት አግኝቶ በ1997 ዓ.ም. አሁን ይፈርሳል የተባለው ቦታ ላይ የአካባቢውን የልማት ዕቅድ በጠበቀ ሁኔታ ከባለአንድ እስከ ባለአራት ፎቅ የሚደርሱ ከ60 በላይ የመኖሪያና የንግድ ድርጅቶች ሕንፃዎችን ገንብተው እንደሚኖሩ ተናግረዋል።እነዚሁ 500 የሚደርሱ ቤተሰቦችና ሠራተኞች እንዳሏቸው የሚናገሩት የላፍቶ ነዋሪዎች ተበድረውና ያላቸውን ጥሪት ጨርሰው የገነቡትን ቤት ‹‹መንገድ የሚያልፍበት ነው›› በሚል ማፍረስ ተገቢ አለመሆኑን ተናግረዋል።

መንገዱ በሌላ በኩል አድርጎ መገንባት እንደሚቻል የሚናገሩት ነዋሪዎቹ፣ የክፍለ ከተማው አስተዳደር ለመንገዶች ባለሥልጣን በአግባቡ ማስረዳት ሲችል ዝም ብሎ በማለፉ ጉዳት ሊደርስባቸው መቃረቡን ገልጸዋል።የመንገድ ጥናቱ የተጠናው ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ውስጥ ሳይሆን የረጅም ጊዜ ጥናት መሆኑን የገለጹት ነዋሪዎቹ፣ የአካባቢውን የልማት ዕቅድ ጠብቆ በተጠና ጥናት የተሰጣቸውን ይዞታ በድንገት ተነስቶ መፍረስ እንዳለበት መናገር ተገቢ አለመሆኑን አስረድተዋል።

ነዋሪዎቹ ያለባቸውን ችግር በማብራራት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ድሪባ ኩማ ያስገቡት ደብዳቤ ለጽሕፈት ቤት ኃላፊው አቶ አሰግድ ጌታቸው መመራቱን፣ እሳቸውም ክፍለ ከተማው አጣርቶ ምላሽ እንዲሰጥ ማድረጋቸውን ጠቁመዋል። ነዋሪዎቹ በድርጅቶቻቸው ውስጥ ከአሥርና ከዚያም በላይ ሠራተኞች እንዳሏቸው፣ ከሽቀጣ ሸቀጥ ሱቆች እስከ ሆቴል ድረስ ያሉ ድርጅቶች እንዳሏቸው በመጠቆም፣ አስተዳደሩ ሥራ አጥን ከመቀነስና የሥራ መስክ ከመፍጠር አኳያ ያለውን ጠቀሜታ፣ እንዲሁም ግንባታውን ያካሄዱበትንና የተፈቀደላቸውን አግባብ በማስተዋል መልካም ምላሽ ሊያገኙ እንደሚችሉ ተስፋ አድርገዋል።

ነዋሪዎቹ እየተቃወሙት ስላለው ሁኔታ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ደስታ ፍጹምን ለማነጋገር በተንቀሳቃሽ ስልካቸውና በቢሮ ስልካቸው የተደወለ ቢሆንም ምላሽ ማግኘት አልተቻለም።

## ወያኔ የምእራብ አርማጮን ነዋሪዎች በሽፍታት ፈርጆ ቁም ስቅል እያሳያቸዉ መሆኑ ተሰማ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮ-ሱዳን ድንበር አካባቢ ምእራብ አርማጭሆ ዉስጥ የሚኖሩ ከሃያ በላይ ቤተሰቦችን ሽፍታ ናችሁ የሚል መሰረተ ቢስ ክስ መስርቶባቸዉ እስር ቤት እንደወረወራቸዉ አማራ ክልል ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘገቢዎች ከስፍራዉ በላኩልን ዜና ገለጹ። በዘገባዉ መሰረት በአካባቢዉ በጥበቃ ላይ የተሰማሩ የዘዘዙ የጸጥታ ኃይሎች በሽፍታነት የጠረጠሯቸዉን ቤተሰብነት ከ20 ያላነሱ ቤተሰቦች አስረዉ እየቀጠቀጡ በማሰቃየት ላይ ናቸዉ። የወያኔ የጸጥታ ኃይሎች ሰላማዊ ኑሯቸዉን የሚኖሩትን የድንበር አካባቢ ሰዎች ቤተሰቦቻችሁ ሽፍተዋልና አሳምናችሁ እጃቸውን ለመንግስት እንዲሰጡ አድርጉ አለዚያም ገድላችሁ ለመንግስት አሳዉቁ በማለት እያሰቃዩዋቸዉ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔ ዘረኝነት፣ በደልና መከራ አንገሽግሿቸዉ የሸፈቱት ግለሰቦች ፍላጎታቸዉ ወያኔን ማስወገድ እንጂ እጅ መስጠት ስላልሆነ የታሰሩት ቤተሰቦቻቸዉ ከፍተኛ ሰቆቃ እየተፈጸመባቸዉ ነዉ።

በእስር ላይ ከሚገኙት የሽፍታ ቤተሰቦች መካከል መልካሙ አዛናው፣ መልካሙ መንግስቱ፣ ብርሃኔ ደምለው፣ ወ/ሮ አረቁ መላሽ፣ ዳኙ ካ ሴ፣ ደስታ ካሳ፣ ገብሬ አዳነ፣ ሁናቸው እና ሌሎች ከ20 በላይ ቤተሰቦች በእስር ላይ ይገኛሉ። በእስር ላይ ከሚገኙት በተጨማሪ ሌሎች ደግሞ አፈናውን በመሰጋት ጫካ ለማደር ተገድደዋል። ጭንቋና በሚባል ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ አረቁ መላሽ ሙቀት የተባለው ልጃቸው በቅርቡ በዚህ ስርአት ውስጥ መኖር አልችልም በሚል መሸፈቱን ተከትሎ፣ ቀሪ ልጆቻቸውን በትነው መታሰራቸውን ለማወቅ ተችሎአል። ግለሰቡዋ የሸፈተው ልጃቸው እጁን እስካልሰጠ ድረስ በእስር እንደሚማቅቁ በፖሊስ ተነግሮአቸዋል።

ከ5 አመታት በፊት የሸፈተውና እስካሁን የመንግስት የጸጥታ ሃይሎች በቁጥጥር ስር ሊያውሉት ያልቻሉት የአበራ ጎባው ቤተሰቦች በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሎአል። አበራ ጎባው ስርአቱን በመቃወም ከሸፈተበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ወጣቶች እየተቀላቀሉት መምጣቱን የአካባቢው ሰዎች ይናገራሉ። ጉዳዩን በማስመልከት በሰሜን አርማጭሆ የአንድነት ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ የሆነውን ወጣት አባይ ዘውዱን አነጋግረነው ነበር። አባይ እንደሚለው ፓርቲያቸው የሽፍታ ቤተሰቦች ተብለው የሚያዙ ሰዎች መኖራቸውን ማረጋገጡንና ብዙ ስቃይ እየደረሰባቸው መሆኑንና መንግስት ለምን በጸጥታ ሃይሎች ሊይዞዋቸው እንዳልቻሉ ገልጿል።

ለሽፍትነት ያበቃቸውን ምክንያትም በስርአቱ በመማረር መሆኑን ወጣት አባይ ይናገራል በሌላ በኩል ደግሞ በመቶዎች የሚቆጠሩ የምእራብ አርማጭሆ ወጣቶች ” ለሱዳንና ለውጭ ኩባንያዎች መሬት እየተሰጠ እኛ ግን የምናርሰው መሬት አጥተናልና መሬት ይሰጠን” የሚል ጥያቄ አንስተው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ከወጣቶች አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ለመረዳት ተችሎአል። ወጣቶቹ ጥያቄቻቸውን ከወረዳ እስከ ዞን ላሉ ባለስልጣናት ቢያመለክቱም ምላሽ አላገኙም። በዛሬው እለትም ለክልል ባለስልጣናት አቤት ለማለት ከ50 በላይ ተወካዮች ወደ ባህርዳር አቅንተዋል። ለሱዳን በተሰጠው መሬት አካባቢ በሱዳኖችና በኢትዮጵያውያን መካከል ግጭት እየተከሰተ መሆኑንም የአካባቢው ሰዎች ይናገራሉ። በቅርቡ አብዱ የሚባል የሱዳን ባለሀብት በኢትዮጵያውያን መገደሉን ተከትሎ ሱዳኖች በወሰዱት እርምጃ ሚካኤል የተባለ የአብረሃ ጅራ ነዋሪ መገደሉን የከተማዋ ነዋሪዎች ይናገራሉ።

## የፋሽስት ወያኔን የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አዲስነትና ድግግሞሽ አድንቀው “ሕዝቡ አሁን ቁርጠኛ ነው” እንዳሉ ዘግቧል።

ከዚህ በፊት በተለያየ ጊዜ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎችና ከተሞች ፋሽስት ወያኔን የሚያወግዙ፣ እየሰራ ያለውን ሀገር የማተፋትና ህዝብ የማደህየት አካሄዱን እንዲሁም ፋሽስታዊ አገዛዙን የሚቃወሙ ጠንካራና ተከታታይ የሆኑ የሕዝብ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በዋካ፣ በአዲስ አበባ፣ በአዋሳ፣ በትግራይ በተለያዩ ከተሞች፣ በደሴ፣ በአርባ ምንጭ፣ በጎንደርና በቅርቡ ደግሞ በባህርዳር ከተማ በግልጽ ባደባባይ የተካሄዱ ሲሆን በህቡዕ ደግሞ ግድግዳ ላይ በሚጻፉ መልክቶችና ሌሊት ሌሊት በሚበተኑ የተቃውሞ በራሪ ወረቀቶች ተቃውሞዎች ሲገለጹ መቆየታቸው ይታወሳል።

## አንድነት ፓርቲ የሚሊዮኖችን ድምጽ ዘመቻዉን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በህዝባዊ ንቅናቄው የአደባባይ ህዝባዊ ስብሰባ እና ሰላማዊ ሰልፍ የሚደረግባቸው ቦታዎች አዲስ አበባ፣ ደሴ፣ ሐዋሳ፣ አዳማ/ናዝሬት/፣ መቀሌ፣ ደብረታቦር፣ ደብረማርቆስ፣ ድሬዳዋ፣ ጂንካ፣ ቁጫ፣አሰሳ፣ ነቀምት፣ ለገጣፎ፣ ወልዲያ፣ ጋምቤላ፣ ምዕራብ አርማጭሆ/ አብርሃ ጅራ/፣ይሆናሉ ብሎአል። አንድነትና መኢአድ ፓርቲዎች በቅርቡ በባህርዳር በብዙ ሺዎች የሚቀጠር ህዝብ ለተቃውሞ እንዲወጣ አድርገዋል። ፓርቲው በመጀመሪያ ዙር የሚሊዮኖች ድምጽ በተለያዩ ከተሞች የተሳካ የተቃውሞ ሰልፎችን ማድረጉ ይታወቃል።

## አንድ ሰዉ ለማዳን አገር አይሞትም

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አገሮችም ዉስጥ ቢሆን አንድ የመንግስት ሰራተኛ ሲታመም ለተወሰነ ግዜ ደሞዝ እተከፈለዉ በራሱ ወጪ ይታከማል፤ ከዚያም ለተወሰነ ግዜ ደሞዝ ሳይከፈለዉ ያገግምና ወደ ስራዉ ይመለሳል እንጂ በዬትኛዉም አገር እስኪሞት ድረስ በህዝብ ገንዘብ የሚታከም የመንግስት ሠራተኛ የለም።

ወያኔ ኦሮሚያ ዉስጥ የራሱን ቡችሎች አስቀምጦ በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሚያደርሰዉን ግፍና በደል አለማየሁ አቶምሳን አንደምሳሌ ወስደን ተመለከትን እንጂ ከትግራይ ዉጭ ሁሉንም ክልል ብንመለከት ለክልሉ ህዝብ እድገትና ብልጽግና የሚሰራ አንድም የክልል ባለስልጣን የለም። ቀድሞዉኑ የክልል ባለስልጣናት ሲሾሙ የሚታየዉ ለወያኔ ያለቸዉ ታማኝነት ነዉ እንጂ ብቃታቸዉና ለህዝብና ለአገር ያላቸዉ ታማኝነት በፍጹም አይታይም። ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ በሚኖርበት አካባቢ መብቱና ነፃነቱ ተከብሮ በሚያምኑበትና በሚያምንባቸዉ ልጆቹ መመራት ከፈለገ ማድረግ ያለበት አንድና አንድ ነገር ብቻ ነዉ፤ እሱም ወያኔንና ዘረኛ ስርዐቱን መደምሰስ ነዉ። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የመጀመሪያዉን እርምጃ የወሰዱ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች አሉና ከእነዚሁ ቆራጥ ጀግኖች ጋር አንድ ላይ ሆነን ወያኔን ለማስወገድ በአንድነት እንነሳ!

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## እነዚህ ሰዎች የሚናገሩትንም አያውቁም !

(ሲሳይ አባተ - ከአዲስ አበባ) - (ክፍል 2 - የመጨረሻ ክፍል)

በመላዋ ኢትዮጵያ እዚያና እዚህ ጉች ጉች ያለ የተንጣለለ የኦሮሚያን ክልላዊ መንግሥት "ከነሙሉ ክብሩና ማዕረጉ በነፃነት ሲያስተዳድር" የነበረ ዕንቁ ዜጋ! አይ ወያኔ። ስንቱን ነው እያሳየን የሚገኘው። ይብላኝልህ አንተ ታሪክ የምትባል ሀገራዊ ደደብ መዝገብ። ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ሀገር ከነዚህ መኸገሮችና ነቀዞች ነፃ ስትወጣ ሀፍረትህ ምንኛ የበረታ ይሆን?

ደንቆሮው ኃይለማርያም ደግሞ ያሳዝነኛል። የተሰጠውን እንዳነበበ "የሥልጣን ጊዜው"ን ሊጨርስ ነው። ምን ዓይነቱ ገልቱ ሰው ነው? እሱም ዛሬ ልክ እንደዚያች የመርገምት ፍሬ እንደአዜብ ጎላ አለማየሁን ‹መስዋእት የሆነ ታጋይ› ብሎት ዐረፈው። የት ዐውደ ውጊያ ሲፋለም ይሆን አቶ አለማየሁ የተሰዋው? በዚህ ብቻም አላበቃም። ለመለስ የተናገረውን ትንሽ ለወጥ አድርገው ጽፈው ሰጡትና "ዘላለማዊ ክብርና ሞገስ ለሰማዕታት" ብሎ ተናገረ፤ አለማየሁም ሰማዕት መሆኑ ነው (ሰማዕት የሚባለውንም ቃል ከሃይማኖታዊው ዐውድ አውጥተን ለዓለማዊ ፍጆታ ካዋልነው በትግል ወቅት የተሰዋ ማለት እንጂ በአገር አማን በበሽታ የሚነጠቅን ዜጋ ለማመልከት አይደለም)። ለውጡ በፊተኛው ጊዜ ይህን መፈክር የተናገረው ለመለስ ነበር። አሁን ግን ለሞቱትና ለመሞት ለተዘጋጁት ለነሳሞራና ሥዩም እንዲሁም ለሌሎቹም ተራቸውን እየተጠባበቁ ላሉ ሚኞች ጭምር ነው። የወደፊቱ ጊዜ የወያኔዎች መረፍረፊያ ጊዜ ነው። (ኢቲቪን አሁን ስመለከት ካህናት ጸሎተ ፍትሃት እያደረጉ ነው። የታደሉ ወያኔዎች ናቸው ጃል! ቤተ ክርስቲያንን ሲፈልጉ ያጠፏታል ሲፈልጉም የማስመሰያ ፍትሃት እንድታደርግላቸው ያስደርጓታል፤ ሁሉ በጃቸው ሁሉ በደጃቸው - ማን ሃይ ሊላቸው። አለማየሁ እየተፈታ ነው፤ ሊያውም ከስንት አድባራት በልዩ ትዕዛዝ በተጠሩ ጳጳሳትና ካህናት። ይሄኔ ተቃዋሚ ቢሞት ኖሮ መንግሥትም ቤተ ክርስቲያንም ያን የሞተ ሰው እንደሥጋት በመቁጠር የውሻ ያህልም ክብር ባልሰጡት። ምን ዓይነት ቤተ ክርስቲያንና ምን ዓይነት መንግሥት ናቸው ያሉን? ያሉ የሚመስሉ ግን የሌሉ። ለሞተም የሚያዳሉና ሙታንንም የሚከፋፍሉ አስገራሚ ጉዶች!)...

ብዕር ካነሳሁ አይቀር በእግረ መንገድ አንድ ሌላ ጉዳይ ላንሳ መሰለኝ። ፕሮፌሰር መስፍንን ምን እየነካቸው ነው? ትናንት አንድ መጣጥፋቸውን ከዘሀበሻ ድረገፅ ላይ አነበብኩ። ጽሑፋቸው ቆንጆ ነው። እንደሁልጊዜው ሁሉ በፍቅር ነው ያነበብኩት። ነገር ግን አንዳንዴ አዝንባቸዋለሁ። ግራ የገባቸውም ይመስለኛል። ግራ ተጋብተውም እኔንም ግራ ያጋቡኛል። ምን ያለ ግራ አጋቢ ዘመን ላይ ደረስን እባካችሁ!

ግንቦት ሰባትን ለምን ትኩር ጥምድ አድርገው እንደያዙት አልገባህ ብሎኛል። እርሳቸው እደግፋዋለሁ በሚሉት ሰላማዊ የትግል ሥልት የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃ ማውጣት እንደማይቻል የተረዱ አልመሰለኝም። የትጥቅ ትግልን እንዳናናቁና ሕዝቡ ለባርነት እንደተጋለጠ በሰልፍና በወረቀት ላይ ብቻ ተወስኖ እየተጯጯኸ ዕድሜውን እንዲጨረስ ይፈልጋሉ መሰለኝ። ምን ማለታቸው ነው? "ያውጡብሽ እምቢ፤ ያግቡብሽ እምቢ" ይባላል እንደዚህ ያለ የማይፈታ ዕንቆቅልሽ ሲገጥም።

መካሪ ማጣት ነው። ወይም ሰውን መናቅ ነው። እንደ አካሄድ ትልቅነት ጥሩ ነው። አባትነት መልካም ነው። ታዋቂነት ደግ ነው። መማር መመራመር ውብ ነው። በሥራ ጉዳይ ሀገርን ተዟዙሮ መቃኘትና ለትውልድ የሚተርፍ ምሁራዊ ትሩፋት ማስገኘት ብዙዎች ተመኝተው የማያገኙት መታደል ነው። በነዚህ ሁሉ ፕሮፌሰሩን አከብራለሁ፤ እወዳቸውማለሁ። ብዙዎች ወገኖቼ እንደሚቸሯቸው ያለ እውነተኛ ፍቅር እኔም ለእኚህ ሀገራዊ ቅርስ አባት አለኝ። ይሁንና ተሰሚነታቸውን በመጠቀም ለሀገር አንዳች ነገር እንሥራለን ብለው ገንዘባቸውን፣ ዕድሜያቸውን፣ ጊዜያቸውንና መላ ትኩረታቸውን የሚያውሉ ወገኖችን ማወክ ተገቢና ወቅታዊም አልመሰለኝም። አንገት የተፈጠረው አዙሮ ለማየት ነው። አዙሮ ማየት ደግሞ በትልቅና በትንሽ ስብዕና የሚወሰን አይደለም። ስህተትን መሥራት በሰውነት ደረጃ የሚገታ እንዳልሆነ ሁሉ ከስህተት ጎዳና ለመውጣት መጣርና ራስን ለመፈተሽ ጊዜና አቅል መግዛትም ለተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ብቻ የሚተው አይደለም። እናም ክቡር ፕሮፌሰር ነገሬን በጥሞና እንደሚረዱልኝ እገምታለሁ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለበትን ሁኔታ የተገነዘቡ አልመሰለኝም። እርሳቸው በፋክት መጽሔት የፈለጉትን ስለተነፈሱና በጡረታም ሆነ በሌላ መንገድ በሚያገኙት (መጠነኛ) ገንዘብ ሕይወታቸውን ከብዙዎች ዜጎች በተሻለ ሁኔታ ስለመሩ ሕዝቡ ተመችቶታል ብለው የሚያስቡ ከሆነ ተሳስተዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለበትን የባርነት ሰቆቃ መረዳት አለባቸው። ችግሩ የአምባገነንነትና የዴሞክራሲ ጉዳይ አይደለም። በነፕሮፌሰር ቀለል ተደርጎ እንደሚገለጠው የዴሞክራሲ ዕጦትና የአምባገነን መንግሥት ጉዳይ የሀገራችን አንገብጋቢ ችግር አይደለም። ይሄን መሰሉ የነፕሮፌሰር ገለጣ ቅንጦት ነው - እዬዬም ሲደላ ነው ወገኖቼ። የኛ ችግር በነፃነትና በባርነት መካከል የሚዋልል የጠበበ አማራጭ ነው። ነፃነቱ ከተገኘ በኋላ ስለአምባገነን መንግሥትም ሆነ ግለሰቦች መነጋገር ይቻላል። አሁን ግን በአፓርታይድና በቅኝ ግዛት ውስጥ በመከራ ሥጋ በመከራ ነፍስ ውስጥ ተጣብቀው እየኖሩ ስለወደፊት አምባገነን ሥርዓት መነጋገር በትንሹ ቂልነት ነው። አለፍ ሲልም ዕብደትና ወፈፌነት ነው። አሁን በሌለ ሥልጣን፣ ባልተገኘ ምቹ ሀገራዊ የሥልጣን አያያዝ ሁኔታ ገና ለገና ግንቦት ሰባት ሥልጣን ይይዝና ጭቆናን ያራምድ ይሆናል ብሎ ሕዝብን ማደናገርና ማደናበር ከሀበሻዊ የምቀኝነት አባዜ ነጻ አለመውጣትን እንጂ ቀናነትን የተላበሰ ሀገራዊ መቆርቆርን አያመለክትም - It is really a far-fetched and more of imaginary concern for the time being. ትግላችን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው አቢይ ትኩረት ይህን በስብሶ ያበሰበሰንንና ተረካቢ ትውልድ ሳይቀር እንዳይኖረን እያደረገን የሚገኘውን የዘረኝነት ሥርዓት አስወግደን ቢያንስ ቢንስ ሁላችንንም በእኩል የሚጨቁን ወይም በእኩል የሚገድል ሥርዓት ማምጣት ነው። ከዚያ በኋላ ያለው ትግል ቀላል ነው። የራሳችንን ጨቋኞች ካገኘን በኋላ ወደ ዴሞክራሲ የሚደረገው ጉዞ በግማሽ አጠረ እንደማለት ነው። አሁን ግን በቅዠት ዓለም እየዋኙ እንደዶክኪሾት በምናብም በእውንም ከሚያስቡትና ከሚያገኙት "ጠላት" ጋር መላተም የህመም ካልሆነ የጤና ሊሆን አይችልም። ያስተዛዝባልም። እንዴ፤ ልብ እንግዛ እንጂ። እስከመቼ አንድ ዓይነት አንቺ ሆዬ ቅኝት እንዘፍናለን? "ሦስተኛውን" ዐይናችንን እንግለጥ።

አንዲት ሴት እንዲህ አለች አሉ - ለባሏ። "ስንደዶ ቀጭቹ፣ አከርማ ቆረጬ ወስከምቢያ ሰፍቼ እሸጥና አንዲት ላም እገዛለሁ። ላሚቱን አስጠቅቼ አርግዛ ስትወልድ ጥጃዋን እዚያች እግገዷ ላይ አስራታለሁ።" ሞኙ ባል ደግሞ "የለም፣ የለም፤ ምን ማለትሽ ነው? እግገኑ ላይማ አናስርም፤ ሰው ይገባል ይወጣል። የሰው ዐይን ደግሞ እንኳንስ ጥጃ ድንጋይ ይሰብራል። ስለዚህ ጓዳ ውስጥ እንጂ እዚህ አናስራትም።" ሚስትዮዋም ቀጠለች፡- "ምን ማለትህ ነው፤ ጓዳ ውስጥማ አናስርም፤ እዚሁ ነው የምናስራት። ደግሞስ አንተን ምን ጥልቅ አደረገህ? ለፍቼ ደክሜ ላሟን እምገዛና አሰጠቅቼ ጥጃዋን እማስወልድ እኔ። ..." ክርክሩ ጦፈ፤ ወደ ከፍተኛ ግጭትም አመራና ባልዮው አጠገቡ የነበረ የቡና ዘነዘና አንስቶ አናቷን በርቅሶ ገደላት - ነፍሷን ይማር። ይታያችሁ - በላም አለኝ በሰማይ ምኑም ምኑም በሌለበት ሁኔታ በባዶ ሜዳ ተጨቃጨቁና ተገዳደሉ። የብዙ ሰዎች ችግር ይህን ይመስላል። የሌለ ሥጋት እየፈጠሩ በማውራትና በማስወራት ከፊት ለፊት የተጋረጠብንን ትልቅ ተራራና አለት በጋራና በቻልነው መንገድ ሁሉ ገፍተን እንዳንጥል ደንቃራ እየሆኑብን ነው። የሚሆነው ሁሉ ከመሆን ባይዘልም እነዚህን መሰል የ"ሳይቸግር ጤፍ ብድር" ዜጎች ወደየጎሊናቸው እንዲመለሱ እንጸልይ። እንቅፋትነታቸው ግልጽ ነውና።

ግንቦት ሰባት ስህተት ሊሠራ ይችላል፤ "እንከን የለሽ ነው። ምሉዕ በኩልሄም ነው" የሚል እምነትም ሆነ አስተሳሰብ የለኝም - በሰዎች ስለሰዎች የሚመራ በመሆኑ ፍጹም ነው ማት አንችልም። ግን ከስህተታቸው እየተማሩ ወደ መልም ዘለቄታ የሚያመሩ ይመስሉኛል። (አንዲት ቀልድ ቢጤ ጣል ላድርግ፤ አንድ ሰው የሚጋልበው ፈረስ ዐመለኛ ኖሮ ተቸግሯል። አልታዘዝለት ብሎ ገደል ሊከተው ደረሰ። ተመልካቾችም አንዳቸው "አንገቱን ያዘው"፣ ሌላኛቸው ልጓሙን ጨብጠው" ደግሞም ሌላኛቸው "እርካቡን እርገጠው" ወዘተ. ሲሉ የሰማቸው ችግር ውስጥ የሚገኝ ሰውዬ "አይ መሬት ያለ ሰው!" አለ አይባላል። ልክ ነው - ያልተነካ ግልግል እንዳለማወቁ ቁጭ ብሎ ወሬ የሚጠርቅ የኔ ዓይነቱ ሥራ ፈት ሰው የሚለው አያጣምና ብዙ ሊፈላሰፍ በዚያ ፍልስፍናውም ብዙ ሊሳሳት ይችላል። ተሳስቶ ከማሳሳት ይሰውረን ወገኖቼ።) በመሠረቱ እኔ የግንቦት ሰባት አባልም ሆነ አቦካቶው አይደለሁም። ግን አዳሜ እየተነሣ የጭቃ ጅራፉን ሲለጥፍበት ያሳዝነኛል - ብዙ የምታዘበው ነገር ስላለ ነው እንደዚህ በምሬት የምናገረው። በእውነቱ የማንሠራና የማናሠራ ዜጎች ብዙ ነን። ባሕርያችን ለያዥ ለገራዥ የሚያስቸግር ክርት ዐመል ያለን ብዙ ነን፤ ምን እንደሚሻለን አላውቅም። አለቃ ገ/ሃና "ለቦና ጥጃ ውስ ምን አነሰው" አሉ አሉ። እናስ ስንትና ስንት የሚወራበትና የሚጨነቁለት ችግር እያለ አሁን በምትወዱት ሞት ይሁንባችሁና ግንቦት ሰባት ለኢትዮጵያ ከወያኔ የበለጠ ራስ ምታት ሆኖ ነው ይህን ያህል ሰዎች እንቅልፍ አጥተውለት ከወያኔ ባልተናነሰ ለውድመቱ የሚቋምጡለት? ከማንም ጋር ይሥራ - የሚያዋጣውን የሚያውቅ ራሱ ነው። ስህተቱን መጠቆም፣ ማረም፣ ማስተማር፣ ማስተካከልና በተቻለ አቅም ሁሉ መርዳት ሲገባ ቤተስኪያን እንደገባች ውሻ ችው ችው ማለት ከአንድ ጤናማ ኢትዮጵያዊ ዜጋ አይጠበቅም፤ ሁል ጊዜ በምቀኝነት አባዜ መጠመድም ተገቢ አይደለም። ትንሽዬ ዝናና ስመጥርነት ስላገኘ ብቻ ባለን የቆዬ የምቀኝነት ባህል እየታወርን ሳቢን ለመግረፍ መጣደፍ አግባብ አይደለምና አንዳንዶቻችን ከምንጓዝበት እርምጥምጥ መንገድ በአፋጣኝ እንውጣ። ቢያንስ ዝም እንበል - ቆርጠን እየቀጠልን በምንፈጥራቸው ስድቦች ሰድበን ለሰዳቢ አንስጠው - "የምታሸንፈውን ምታ" ቢሉት ወደ ሚስቱ እንደሮጠው ፈሪ ባል ወያኔ ሲያቅተን በዚህ የትናንት ድርጅት አንረባረብ፤ ባይሆን ወፌ ቆመች እንበለውና የበኩሉን እንዲጥር እናግዘው። ከፈራነውም አሁኑኑ በእማኞች ፊት እናስፈርመውና ሥልጣኑን ከወያኔ እንደቀማ - ህልሙ ተሳክቶለት መቀማት ከቻለ - ሕዝብ ለሚመርጠው ሰው እንዲያስረክብ ቃል እናስገባው። በበኩሌ ምነው ግንቦት ሰባት በተሳካለትና በኢትዮጵያዊ አምባገነን በተገዛሁ እላለሁ። የራሴን አምባገነን መታገል እመርጣለሁ በባርነት የአፓርታይድ ሥርዓት ውስጥ ከሰውነት በታች ሆኜ ከምኖር። የምርጫ ጉዳይ ነው። ግንቦት ሰባት በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሊሠራቸው በሚችላቸው ስህተቶች ምክንያት በጭካኔና በኢዴሞክራሲያዊነት ከወያኔ ጋር መፈረጅ የጤና አይመስለኝም። በእግረ መንገድም ኢሳትን ከግንቦት ሰባት ጋር እያያያዙ ይህን የሕዝብ ብሶት መተንፈሻ ጣቢያ እንዲጠላ የማድረግ ዘመቻ አሁኑኑ ማቆም የሚገባ ይመስለኛል። ኢሳትን ሲዘልፉትና ሲሰድቡት ስሰማ እነዚህ ሰዎች በተጠናወታቸው ሥነ ልቦናዊ ደዌ አዝናለሁ። ከወያኔ ምንዳ ተቀብለው ይሆን ብዬም ለማሰብ እገደዳለሁ። ኢትዮጵያውያን እንደዚህ ዘመን ከፉኛ የተከፋፈልንበትና በጦዘ የርስ በርስ ቅራኔ የገባንበት ዘመን ይኖር ይሆን? ለማንኛውም ስንናገርና ስንጽፍ ከአንዴ በላይ አሰብ እያደረግን ቢሆን መልካም ነው። ወደ ቀብር ልሄድ ነው - ቻዎ።

## ሀረር ዉስጥ የደረሰዉን ቃጠሎ የተቃወሙ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በቁጥጥር ስር መዋላቸውን አምነዋል። የክልሉ ፖሊሶች የእሳት ቃጠለው በደረሰበት አካባቢ በስፋት ተሰማርተው የሚገኙ ሲሆን፣ዘገባውን እስካጠናከርንበት ጊዜ ድረስ የተወሰኑ ትምህርት ቤቶችም ተዘግተዋል።አብዛኛው የከተማው ነዋሪ የእሳት አደጋው መንስኤ የክልሉ መስተዳድር ነው የሚል እምነት ሲኖረው መስተዳድሩ በበኩሉ በህዝቡ የሚቀርበውን ክስ አይቀበልም። በከተማው ባለፈው እሁድ የተነሳው የእሳት ቃጠሉ ከፍተኛ የንብረት መውደም ማስከተሉ ይታወቃል። ሀረር ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር እና መሰረታዊ የሆኑ ፍላጎቶች እጥረት እንዳለባት ነዋሪዎች በተደጋጋሚ በምሬት ሲገልጹ ቆይተዋል።

ንደተመለከተው "ፕሬዚደንቱ የይቅርታ ቦርድ የውሳኔ ሃሳብን መሰረት በማድረግ ይቅርታ ይሰጣል" ይላል።ይቅርታ በሚሻርበት ወቅትም ፕሬዚደንቱ ማየት ሳያስፈልገው በቦርዱ ውሳኔ ብቻ እንዲፈጸም በአዲሱ ረቂቅ አዋጅ ተደንግጎአል። በክልል የሚገኙ ታራሚዎችን ጉዳይ በአጭር ለመቋዋጨት ሲባል ፕሬዚደንቱ ስልጣኑን በውክልና ለክልሎች እንደሚሰጥ ተደንግጎአል። በዚህ ማሻሻያ ህግ መሰረት ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሳኔ መሰረት ፍርደኞች ይቅርታ ከጠየቁ በዚህ ሕግ እንደሚዳኙ ተመልክቶአል።የይቅርታ ቦርዱ አባላት ካልነበሩ አካላት መካከል የፌዴራል ፖሊስና የመከላከያ ምክትል ዳይሬክተር እና ሚኒስትር ዴኤታ በቦርዱ እንዲካተቱ አዋጁ ይፈቅዳል። ሽብርተኝነት፣ በመሰረተ ልማት አውታር ላይ የሚፈጸም ወንጀል፣ ሕገወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር፣ሙስና፣ግብረሰዶማዊነት፣የመድፈር ወንጀል እና የመሳሰሉት ይቅርታ የማያሰጡ ተብለው ከተዘረዘሩት ወንጀሎች መካከል ይገኙበታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከሰሞኑ ከሀረር በሚደርሱን መረጃዎች መሰረት በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠረውን ንብረት ያወደመውን እሳት የመስተዳድሩ ባለስልጣናት ሆን ብለው አስነስተውታል በሚል የተቆጡ ብዛት ያላቸዉ ከአገዛዙ ጋር ለመፋጠጥ በዝግጅት ላይ መሆናቸዉ ታወቀ። መስተዳድሩ በአፋጣኝ ለወደመው ንብረት ተገቢውን ግምትና ካሳ ካልሰጠ ለአመታት የተጠራቀመው ብሶት ወደ አላስፈላጊ ግጭት ሊያመራ ይችላል በማለት ነዋሪዎች ከዝግጅት ክፍላችን ስልክ እየደወሉ በመናገር ላይ ናቸዉ።